## ይህ ቢሆንስ? ...

- ብድር ለማግኘት ሲያመለክቱ የማመልከቻ ቅጽ ወይም አስፈላጊ የሆነ መረጃ ተከልክለው ያውቃሉ?
- ብድሩን በተመለከተ ከአበዳሪው ጋር ባሉት ገንዘብ የማግኘት አማራጮች ላይ ውይይት አካሂደዋል?
- ለብድር ጥያቄዎ አፋጣኝ ምላሽ አልተሰጦትም?
- ከብድሩ ጋር ተያያዥነት የሌለው መረጃ ለማግኘት ሲባል ለብድር ጥያቄዎ ምላሽ ዘግይቶቦታል?
- አበዳሪው ብድር የማግኛ መስፈርቶቹን ሳያማክሮ ወይም ሳያወያዩ ቀይሯቸዋል?

ብድር ወይም ብድርን ለማግኘት የሚረዱ መረጃዎችን በመከልከል እንዲሁም የብድር መስፈርቶችን እና ሂደቶችን በተመለከተ የተሳሳተ መረጃ በመስጠት መድሎ ማድረግ በሕግ ያስጠይቃል።

ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሕጋዊ ያልሆኑ የቤት መድሎዎች ሲሆኑ በዲ.ሲ. የሰብአዊ መብቶች እንዲሁም በቤቶች አስተዳደር ሕግ የተከለከሉ ናቸው።

**ከላይ የተዘረዘሩት በደሎች ከተፈፀመቦት ጉዳዩን በሚከተለው አድራሻ ለዲ.ሲ. የሰብአዊ መብቶች ጽ/ቤት ያስታውቁ። ስልክ (202) 727-4559**



የወለድ አገድ የብድር አገልግሎት ለማግኘት ሲጠይቁ አግባብ ያልሆነ መድልዎ ተደርጐቦት ከሆነ በሚከተለው አድራሻ ያመልክቱ።

**የሰብአዊ መብቶች ጽ/ቤት**
(202) 727-4559 ወይም www.ohr.dc.gov

ወይም

**የአሜሪካ የቤቶች እና የከተማ ልማት መምሪያ**
1-800-424-8590

በመጭበርበር ምክንያት ብድር ያገኙ ከመሠለዎት እባክዎን በዚህ አድራሻ ያግኙን፡

**የዲሲ የባንኪንግ እና የገንዘብ ተቋማት መምሪያ**
(202) 727-1563

**የፌዴራል ሪዘርፍ ባንክ**
(202) 452-3693

ይህ ባንክ የሀገሪቱን የገንዘብ እና የባንኪንግ ሥርዓት ደህንነትና ህልውና ለመጠበቅ የባንክ አገልግሎት በሚሰጡ ተቋማት ላይ ቁጥጥር ያደርጋል።

**የፌደራል የንግድ ኮምሽን**
1-877-FTC-HELP (382-4357)

የፌደራል የንግድ ኮምሽን የገንዘብ ማጭበርበርን፣ ማታለልን እና ሕገ ወጥ የሆኑ የንግድ አሠራሮችን ለማስወገድ የፌደራል የተጠቃሚዎች ሕግን ተግባራዊ ያደርጋል።

### ስለ እኩል መብት የተሰጠ መግለጫ

እ.ኤ.አ. በ1977 በወጣው የዲ.ሲ የሰብአዊ መብቶች ሕግ እንዲሁም በተሻሻለው የዲ.ሲ. ይፋዊ ሕግ አንቀጽ 2-1401.01 መሠረት የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የዘር፣ የቀለም፣ የሐይማኖት፣ የብሔር፣ የፆታ፣ የዕድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የመልክ፣ የወሲብ ዝንባሌ፣ የቤተሰብ ደረጃ፣ የቤተሰብ ኃላፊነት፣ የትምህርት ደረጃ፣ የፖለቲካ፣ የአካል ጉዳተኝነት፣ የገቢ ወይም የመኖሪያ እና የንግድ ቦታ መድልዎ አያደርግም። በተጨማሪ ሕጉ የወሲብ ጥቃትን እንደፆታ መድሎዎ በመቁጠር ድርጊቱን ይቃወማል፣ ይከለክላልም። ይህን ሕግ መጣስ ያስቀጣል። ግዛቱ ሕጉን በማያከብሩ ነዋሪዎች ላይ አስፈላጊውን የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ይወስዳል።

የአሜሪካ የቤቶችና የከተማ ልማት መምሪያ ይህ በራሪ ወረቀት እንዲዘጋጅና እንዲታተም የገንዘብ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ቤት የማግኘት ህልምን እውን ማድረግ



# በክፍለ ግዛቱ እኩል የሆነ የብድር አገልግሎት ሥርዓት ማስፈን

## በአድሎ እና በማጭበርበር ላይ የተመሠረተ የብድር አሰጣጥን ማስወገድ

**የሰብአዊ መብቶች ዲ.ሲ. ጽ/ቤት**
441 4th Street N.W., Suite 570N
ወይም
3220 Pennsylvania Avenue S.E.
Washington, D.C.
(202) 727-4559

## ተገቢ የሆነ ብድር ምንድን ነው?

**የፌደራል ቤት የማግኘት እኩል መብት እና ዲ.ሲ. የሰብአዊ መብቶች ሕግ በኮሎምቢያ ክፍለ ግዛት ቤት በማግኘት መብት ላይ መድልዎ ማድረግን ይከለክላል::**

**ቤት የማግኘት እኩል መብት (42 ዩ.ኤስ.ሲ. 3601፣ እ.ኤ.አ. በ1968 የታወጀው የሰብአዊ መብቶች ሕግ አንቀጽ 8 እንዲሁም እ.ኤ.አ. በ1988 የተሻሻለው የቤቶች አስተዳደር ሕግ) ዘርን፣ ቀለምን፣ ብሔርን፣ ሐይማኖትን፣ ፆታን፣ አካለ ስንኩልነትን፣ የቤተሠብ ደረጃን (ማለትም ከ18 ዓመት በታች የሆኑና ከወላጆቻቸው ወይም ከሕጋዊ ሞግዚቶቻቸው ጋር የሚኖሩ ልጆችን፣ እርጉዝ ሴቶችን እንዲሁም ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆችን የሚያስተዳድሩ ዜጐችን ጨምሮ) በመመርኮዝ በቤቶች ሽያጭ፣ ክራይ ወይም ግንባታ ወቅት የሚደረጉ መድሎዎችን ይከለክላል::**

**እ.ኤ.አ. በ1977 የተሻሻለው የዲ.ሲ. ሰብአዊ መብቶች ሕግ የፌደራል የቤቶች አስተዳደረ ሕግን ያጠናክራል:: በተጨማሪም ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ጉዳዮች የሕግ ከለላ ይሰጣል፤ ዕድሜ፣ የጋብቻ/የቤተሠብ ሁኔታ፣ ፍትወተ ዝንባሌ፣ የመኖሪያ/የንግድ ቦታ፣ የቤተሠብ ኃላፊነት፣ የፖለቲካ አቋም፤ የትምህርት ደረጃ እና፣ የገቢ ምንጭ::**

### የማጭበርበር ብድር ማለት ምን ማለት ነው?

ይህ ዓይነቱ የማጭበርበር ብድር በብዛት የሚከሰተው በወለድ አገድ እና በሸማቾች የብድር አገልግሎት ዘርፍ ሲሆን፤ በተጭበረበረው የብድር አገልግሎት ተገልጋዮች ለከፍተኛ ወጪ ይዳረጋሉ:: እንደዚህ ዓይነት ብድሮች የቤት ባለቤቶችን ንብረታቸውን ያሳጣቸዋል::

ለቤት መሥሪያ የሚሆን ብድር ለመውሰድ፣ ቤት ለመግዛት ወይም በቤቶ ላይ የማሻሻያ ግንባታ ለማካሄድ ሲፈልጉ እነዚህን የተጭበረበረ ብድር በመስጠት የተሰማሩ አበዳሪዎች ገንዘቦትን ብሎም ደግሞ ቤቶትን ጠቅልሎ ከመውሰድ ሁሌ ዝግጁ ናቸው:: ይህ ዓይነት ብድር ለአበዳሪው ከፍተኛ ትርፍ የሚያስገኝ ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ ተበዳሪውን በቀላሉ ሊወጣበት ከማይችል የብድር እና የዕዳ ችግር ውስጥ የሚጨምር ነው::

### እነዚህ አጭበርባሪ አበዳሪዎች የማያነጣጥሩት በማን ላይ ነው?

አጭበርባሪ አበዳሪዎች በአብዛኛው የሚያነጣጥሩት የብድር ችግር ባለባቸውና ጥሬ ገንዘብ በሚፈልጉ የቤት ባለቤቶች ላይ ነው::

እነዚህ አበዳሪዎች ገንዘብ ለሚፈልጉ፣ የአገልግሎት ወይም የሕክምና ወጪያቸውን መሸፈን ላልቻሉ እንዲሁም መኪናቸውን እና ቤታቸውን ማሳደስ ላቃታቸው የቤት ባለቤቶች ማስታወቂያ ያወጣሉ::

ከዚህ በተጨማሪ አጭበርባሪ አበዳሪዎች አዛውንቶች እንዲሁም በዝቅተኛ ገቢ እና ደመወዝ ባላቸው የቤት ባለቤቶች ላይ ያነጣጥራሉ::

### ቤት የመግዛት ሥርዓትን በሚመለከት የአካባቢዎን የቤት ምክር ሰጪ ድርጅት ይገናኙ::

## አጭበርባሪ አበዳሪዎች በምን ይታወቃሉ?

**አጭበርባሪ አበዳሪዎችን ከእውነተኞቹ የሚለያቸው በርካታ ባሕሪያት አላቸው:: እነዚህን ባህሪያት ጠንቀቆ ማወቁ የነዚህ ግለሠቦች የማጭበርበር ሰለባ እንዳይሆኑ ይረዳዎታል::**

1. ብድር ለማግኘት መረጃ እንዲያጭበረብሩ ሲነገሮት ሠነዱ ላይ ፈጽሞ እንዳይፈርሙ::
2. አበዳሪው ከሚፈልጉት እና መክፈል ከሚችሉት በላይ ብድር እንዲጠይቁ ያበረታታቸዋል::
3. አበዳሪው ግልጽ ያልሆኑ ወይም ያልተጠናቀቁ ቅፆችን እንዲፈርሙ ይጠይቆታል::
4. አበዳሪው የፈረሙበትን ሠነዶች ኮፒ ማግኘት እንደማይችሉ ይነግሮታል::
5. አበዳሪው በመጀመሪያ የሆነ ሃሳብ ያቀርባል:: ቀስ ብሎም ተበዳሪው ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቁ ውሎችን እንዲፈርም ግፊት ያደርጋል::
6. «ሥራ እና የብድር አገልግሎት የሎትም? አይጨነቁ የቤቶን ካፒታል በማስያዝ በቀላሉ ብድር ሊያገኙ ይችላሉ::» የሚሉ የደብዳቤ እና የቴሌቪዥን ማስታወቂያዎችን በጥልቀት ይመርምሩ:: ያስታውሱ! ሁኔታው ሊያምኑት ከሚችሉት በላይ ከሆነ ከአበዳሪው ይራቁ::
7. አዳኝ አበዳሪዎች የተበዳሪዎን የመክፈል አቅም ሳያገናዝቡ ያበድራሉ:: ይህ ደግሞ በስተመጨረሻ የተበዳሪው ንብረት በወለድ አገድ እንዲያዝ ያደርጋል::
8. አዳኝ አበዳሪዎች የአገልግሎት ክፍያዎን ለመሸፈን ሃሳብ እስከማቅረብ ሊደርሱ ይችላሉ::

